*ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ*

*Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity*

Efdpu@aol.com www.Finote.org

*የፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ ሀተታ*
*ግንቦት 22 ቀን 2007 ዓ.ም. የተላለፈ*

# አለ ነገር!

ሞኝን ሰው እባብ ሁለቴ ይነክሰዋል ተብሏል፡፡ ሁለቴ የሚሞኝ ሕዝብ ሊኖር አይችልም ማለቱ ከከበደ ቢያንስ አይገባም ብንል ትክክል ይሆናል፡፡ በየካቲት 66 ሕዝብ ድሉን ተቀማ፣ በ1983ም ይህ ቅሚያ ተደገመበት፡፡ በ1997 ደግሞ ሕዝብ ድምፁን ተቀማ፣ ጭፍጨፋ ደረሰበት በግንቦት 2002 ተደገመ፡፡ በመጭው ምርጫ ተብየው ለውጥን መጠበቅ ደግሞ ከሞኝነት ክልል የወጣ ከባድና ሀገርን ጎጂ ጥፋት መሆኑ የሚያከራክረን አይደለም፡፡

በቅድሚያ በሀገራችን ያለውን ተጨባጭ የፖለቲካ ሁኔታ ስንመረምር ከወያኔው ቡድን ድንፋታ ና ቀረርቶ ባሻገር ስርዓቱ ተበለሻሽቶና በስብሶ መገኘቱን፣ ቀባሪውን እየጠበቀ ያለና ሙት አፋፍ የደረሰ መሆኑን መገንዘብ እንችላለን፡፡ ይህን ማለት ከጀመርን የተወሰኑ ዓመታት መቆጠራቸው ው የድምፃሜውን ሀቀኝነት የሚለውጥ አይሆንም፡፡ የፖለቲካ ሁኔታን በየፈርጁና በተለይም ከላይ ገኖ እዩኝ አዩኝ ከሚለው ባሻገር መሰረታዊ ይዘቱንና አቅጣጫውን መመርመር የሚሳናቸ ው ክፍሎች በግልቡ ይመለከቱና አገዛዙ ጠንካራ ነው፣ ይኸው በስልጣን ቆየ አይደል፣ ይኸው ተቃዋሚ የሚባሉት ተፍረከረኩ አይደል፣ ጀግና ጠፋ እኮ ወዘተ የሚሉ የቀቢፀ ተስፋ ድምፃሜዎ ችን ሊያሰሙ ይችላሉ፡፡ ይህ ግን ስህተት ነው፡፡ አንድ አገዛዝ ቀፎው ቀርቶም በስልጣን መቀጠሉ ጥንካሬውን አያሳይም፡፡ የስርዓቱን መሰረት ማለትም ጥንካሬ ድክመቱን ማጤን ያስፈልጋል፡፡ እየተንገዳገደ መቀጠሉ ረጅም ዕድሜን ሳይሆን ለውድቀቱ ወሳኝ የሆኑት ሌሎች ጉዳዮች ገና አ ለመሟላታቸውን ነው የሚጠቁመው፡፡ የወያኔ አገዛዝ የብዙሃኑ ድጋፍ የለውም፡፡ በብሄረሰብና ዘ ረኝነት ደረጃ ወያኔ ከጎኔ አቁሜዋለሁ በማለት የሚፎክርበት የትግራይ ሕዝብ እንኳ ራ በአብላ ጫው የሚደግፈው አይደለም ቢባል ስህተት አይደለም፡፡ በእርግጥ ይህ ጉዳይ ውስብስብ ስለሆነ ጠለቅ ያለ ትንተናንና አያያዝንም መጠየቁ ባይቀርም ፀረ ወያኔውን ትግል ከተፈፋመ ብዙሁኑ የትግራይ ተወላጅ ለወያኔ አገዛዝ ደጋፊ ሆኖ አይቆምም ማለቱ ትክክል ነው፡፡ የወያኔ ቡድን በሕ ዝብ ተቀባይነትን አግኝቶ በስልጣን ሊደላደል አልቻለም፡፡ ይህ ዋነኛው ድክመቱ ነው፡፡ ሕዝብን በጎጥና በሀይማኖት በመከፋፈል ደረጃ የተወሰነ ድል አግኝቶ የሀገሪቷን ህልውና ለአደጋ ቢያጋል

ጥም ጭቁኖች ከጎኑ ከቶም አልተሰለፉም፡፡ ዴሞክራሲና ዕድገት አመጣሁ የሚለው ቅጥፈት መ
ሆኑ በሀገርም በዓለም አቀፍም ደረጃ ታውቋል፡፡ በፖለቲካው መስክ ኪሳራው በራሱ ድርጅት መ
ከፋፈልም የተከሰተ መሆኑ ታይቷል፡፡ይህ ኪሳራም በኤኮኖሚው መስክም ገሀድ ወጥቶ ሚሊዮኖ
ች ለረሀብና ለመከራ የተጋለጡበት ስርዓት መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን በሙስናና ዝርፊያ ፀረ ኢት
ዮጵያ መሆኑንም አሳይቷል፡፡ የባዕድ ቅጥረኝነቱና ወራዳነቱ ደግሞ ይበልጥ በሕዝብ ያስጠላው ሲ
ሆን የሀገርን መሬትና ክብር ለባዕድ መሸጡ ደግሞ የወያኔን አገዛዝ በኢትዮጵያ ታሪክ ከታዩት ፀ
ረ ኢትዮጵያ አገዛዞች  ሁሉ የባሰ መሆኑን ለታሪክ መዝግቦበታል፡፡

አንድ አገዛዝ ወይ ስርዓት ጠንክሯል ወይም ተደላድሏል የሚባለው በጦርና አፋኝ ሀይሉ ብቻ
ተማምኖ በስልጣን መንገዳገዱ ሳይሆን መሰረታዊና ሰፊ ደጋፍን በሁሉም መስክ ከሕዝብ አግኝቶ
አይበገሬ ሲሆን ነው፡፡ ስልጣኑን በሀይል ብቻ ከጠበቀ ራሱ የሽንፈቱ ማረጋገጫና የውድቀቱ ቀን
መጀመሪያ ነው ማለት ይቻላል፡፡ የወያኔ አገዛዝ ከዓመት ዓመት እየከሰረና እየተጋለጠ ፣የሚያምፅ
በት ሕዝብ ቁጥር እየጨመረ ፣ፖለቲካዊና ኤኮኖሚያዊ ዕቅዶቹ ሁሉ እየተፋለሱበት በመሄድ
ላይ ነው፡፡ ወድቀቱ ጊዜን የፈጀ ቢሆንም ከውድቀት አፋፍ ላይ ነው ቢባል ትክክል ነው፡፡ ገፊ
ግን ያስፈልገዋል፡፡ አለ ነገር ከወያኔ መንደር ባለ አፋችን አለ ነገር በእኛውም ሰፈር ማለት
መገደዳችን አልቀረም፡፡ በዚህ በሕዝብ ጎራ በበኩል ያለው ድክመት የሚካድ አይደለም፡፡ ይህን
በተመለከትም በተደጋገሚ ትችትና ማሳሰቢያ  መሰንዘሩ ይህ ድክመት ወሳኝ ሆኖ ለድል አላበቃ
ን በማለቱ የተነሳ መሆኑ መታወቅምአለበት፡፡ ይህ ለምን ተነስቶ የሚሉ ክፍሎች ለትግሉ አይጠ
ቅሙም፣ ሆድ ይፍጀው አቅዋማቸው ሆዳችንንም መላ አካላታችንንም አቃጥሎ ይጨርሰናል
እንጂ ! የወያኔ አገዛዝ ጠንክሮና አይሎ አልወድቅ ብሎ አላቃተንም-- ልንጥለው ጠንክረን
መታገሉ አቅቶን እንጂ! ለዚህም ነው  እንዴት ለምን ብለን በጥልቅ መመርምር ያለብን፡፡ ጠነከር
ኩ ያለውን ለማዳከም ድክመታችንን አስወግደን መጠንከር መቻል አለብንና፡፡  የወያኔ ቡድን
ባለው ፀረ ኢትዮጵያ ጥላቻ ታውሮ ብዙ ከሕዝብ ሊታረቅ የሚችልበትን ዕድል አፈር አብልቷል፡
፡ የዘረኛ ዕብሪቱ አሸንፎት ራሱን በራሱ አዳክሟል፣ በራሱ ላይ ዘላቂ ችግሮችን ፈጥሯል፡፡ ጠቦ
መሰረቱን አጥብቧል፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ ራሱን አጋልጧል፡፡ በዚህም መንገድ ለጠላቶቹ
የሚጠቅሙ ብዙ ሁኔታዎችን ፈጥሮ ይገኛል፡፡ ዛሬ የወያነ ቡድን አረመኔና ፀረ ሕዝብ ነው ብሎ
ቅስቀሳ አያሰፈልግም፡፡ ዘረኛና ኋላ ቀር ነው ብሎ ማሳመንን አይጠይቅም፡፡ ረሀብና ችግር ቀፍቃ
ፊ ነው ብሎ መከራከር፣ ዜጎችን ለችግርና ለስደት ያበቃ ነው ብሎ ማስርዳትን ግድ አይልም፡፡ኢ
ትዮጵያን የሚቆራርጥና የሚሸጥ ባንዳ ቡድን ነው ብሎ ማስረዳትም አያስፈልግም፡፡ ሕዝብ አው
ቆታል፡፡ ከዚህም አልፎ ይህ አረመኔ አገዛዝ በሁለገብ ትግል--ነገ ሳይሆን ቢቻል ትላንትም ቢሆን

-- በተቻለው መንገደ ሁሉ መወገድ መውደቅ እንዳለበትም ብዙሀኑ አምኗል። ይህ በጠላቶቹ ቅ ስቀሳ ብቻ ሳይሆን በራሱ ጥፋትም የተነሳ የተከሰት ሀቅ ነው።

የወያኔ አገዛዝ ቀውስ በጣም ጥልቅና በጥገና ለውጥ የሚፋቅ አለመሆኑ ግልፅ ነው። ይህ ቀውስ ለመሰረታዊ ለውጥ አዋላጅ እንዲሆን ግን ሕዝብ ባለፈውና በገለማው መንገድ አልገዛም ማለቱ ብቻ ሳይሆን ይህን እምቢታውን የሚገልጥበት የተደራጀ ይዘት ያስፈልገዋል። የታሪክንም መኪና ሕዝብ በፈለገበትና በተመኘበት እንዲነዳ ከታሰበ ድርጅት ሊኖረው ይገባል። ድርጅት ስጡኝና ሀገሪቷን ልለውጣት ተባለ የሚለው ይህን መንፈስ የሚያንፀባርቅ ነው። ድርጅት ሲሉ ድርጅት ስንልም እዚህ ላይ ከጉዞአችን ጎዳና ላይ ገጭ ብሎ ምላሽን ይጠይቀናል። የተደራጀው ባልተደራጀው ላይ የበላይነት እንደሚኖረው በየካቲተ 66ም በግንቦት 1983ና ግንቦት 1997ም ተረድተናል። መደራጀት ሰንልም ራስን ደርጅት ነኝ ብሎ መሰብሰቡ ብቻ በቂ አይለደም። ተለጣፊም ድርጅት ነው። ስርዓቱንም በእጅ አዙር ለማዳን በሆነ መድረክ መደራጀት ይቻላል። ተደራጅቶ ለባዕድ ማደርም የታየና አሁንም ያለ ነው። ተደራጅቶ የተደራጁትን መከፋፈልና ለማዳከም መጣርም ዋና መርህ ግብርን አድርጎ የበጥባጭ ህልውናንም መያዝ ይቻላል--ታይቷል ም። ስለዚህ ሕዝብ ይደራጅ ወይም ድርጅት ያስፈልገዋል ስንል ለሕዝብና ሀገር መሰረታዊ ጥቅም የቆመ ድርጅት ወይም ድርጅቶችን ለመጠቆም ነው። የነዚህንም ሀቀኛ ይዘት መለየት የምንችለው በሚያወጡት መርህ ግብር ወይም ስለ ራሳቸው ማንነትና ይዘት ራሳቸው በሚለፍፉ ት ሳይሆን ተግባራቸውን ተጨባጭ ሰልፋቸውን/አቅዋማቸውን በጥሞና በመመርመር ነው። አሊያማ በአሁኑ ጊዜ ራሱን ዴሞክራሲያዊ ወይም ሕዝባዊ የማይል ድርጅት መቼሰ ተፈልጎ ይጠፋል? ድርጅቱ የሕዝብን ጥቅም አስቀደሞ የሚታገል መሆኑ ከተረጋጋጠ ወይም ሊታገል ሲጥር ከታየ እውን ይህን ድርጅት ወይም መሰል ድርጅቶች ለሕዝብ የቆሙ ነው/ናቸው ማለት ይቻላል። የሕዝብ ድርጅት ስንልም ከሕዝብ ቀድሞ ያልተስፈነጠረ ወይም ዳተኛ ሆኖ ከሕዝብ ኋላ የሚጎተት መሆን የለበትም። ድርጅተ የመሪነት ሚናውንና በሕዝብም የመመራት ግዳጁን በሚዛን ይዞ ለመታገል መቻል አለበት። ድርጅት ቅርበቱ ከሕዝብ ይልቅ ከአገዛዝ ጋር ከሆነ አጠያያቂ ሁኔታ ይከሰታል። የድርጅት መሪዎች ቆራጥነት ሲባልም ከዚሁ ተያይዞ የሚታይ ነው ።የሕዝብ ታማኝ የሆነ ድርጅት ዋና ፍላጎቱና ግቡ የአገዛዙን ወድቀት ለማየት፣ለማምጣት ነው። የአገዛዙን ድምጥማጥ መጥፋት የማይፈልግና ለዚሁም ግብ አምርሮ የማይዋደቅ ድርጅት የሕዝብ ድርጅት ሊባል አይችልም።

በአገዛዙ ላይ ሊኖረን የሚገባው እይታ በአሜሪካ ወይም እንግሊዝ ወይም በወያኔ ቡድን የሚወሰን ወይም የሚቃኝ ሊሆን አይችልም። አገዛዙ በሕዝብ አመፅና እምቢታ ሲናጥ የተቃዋሚ ድርጅቶ

ች አብረውት ሊርዱ አይጠበቅም--ሊፈነድቁ እንጂ:: የተቃዋሚ ድርጅቶች ተልዕኮ የአገዛዙን ቀውስ ማባባስ ብቻ ሳይሆን ቀውስም መፍጠር ነው:: ቀውስ ወይም ችግሩ ሲያጋጥመው ደግሞ ይህን በማጉላት የአገዛዙን ክስረትና ፀረ ሕዝብነት ይበልጥ ማጋለጥ ይገባቸዋል:: የወያኔ አገዛዝ የኑሮ ውድነትን ሰማየ ሰማያት ሲያደርስ፤ ሕዝብ ሲቸገር ሲጠማ፤ ሕዝብ በችግር ምክንያት ከሀገሩ ሲሰደድ በባእድ የሚከላከልለት እጥቶ ደሙ እንደጎርፍ ሲወርድ፥ የአገራችን መሬት ለባእዳን ሲቸበቸብ፤ ሕዝባችን ከቀየው ሲፈናቀል ወዘተ... ተቃዋሚ ድርጅቶች አገዛዙን ማጋለጥና መታገል ይኖርባቸዋል:: የእንዱን ድርጅት አባል ሲያስር ሲያዳክም ድርጅትቶች ሕዝብን አስተባብረው ተቃውሞውን ማፋፋም፤ ሕዝብን ለአመፅ ማነሳሳት ይጠበቅባቸዋል:: አቢይ ችግሮች እየተከሰቱ ተቃዋሚ ሀይል ነኝ ባዮች ዝምታን ከመረጡ ተቃዋሚነታቸው ምን ላይ ነው? ህይወት ዘርተው ድርጅታዊ ህልውናቸውን የሚያሳዩት መቸሊሆን ነው? ወያኔን በምርጫው በማጀብ?!

በዚህ መስፈርትና መመዘኛ መሰረት ተቃዋሚና የአገዛዙን አጃቢ ማንነት መለየት የምንችል ሲሆን በተለይ ደግሞ ቀደም ሲል ካነሳነው ተመክሮ አንፃር ማለትም ከግንቦት 1997 ኡ ምርጫ ተመክሮ ስንነሳ ያኔ የሕዝብን ድምፅ ስረቆና አፍኖ፤ ከ 200 በላይ ንፁሐንን ገድሎ፤ ከ 50 ሺ ያላነሱትን ለእስር ዳርጎ በስልጣን የቀጠለው ወያኔ ዛሬ በግድም በጥቅምም የመለመልከኣቸው አባሎች 6 ሚሊዮን አልፈዋል እያለና ዛሬም የምርጫ ህጉና ኮሚሽኑን ለራሱ በሚመች ባደረጀበት ሁኔታ ነፃ ምርጫ ይካሄዳል ብሎ ማለም ቅዠት መሆኑ ግልፅ ነው:: ለዚህም ነው ሀቀኛ የሕዝብ ድርጅቶች በዚህ የወያኔ ምርጫ መሳተፍ የማይገባቸውና ወያኔ ከተለጣፊዎቹ ጋር እርቃኑን እንዲቀር ማድረግ የሚገባቸው:: በወያኔ መጪው ምርጫ መሳተፍ መፍጨርጨር ወይም ለሰላማዊ ትግሉ መሟሟት ሳይሆን ለወያኔ አገዛዝ ማጭበርብር አጋዥና ተባባሪ መሆን ነው:: በሀገራችን ነፃ ምርጫ ሊካሄድ የሚችለው የሕዝብ ዴሞክራሲያዊ መብቶች ሲከበሩ ነው:: በአርግጥ ምርጫ መካሄዱ በራሱ ብቻ ዴሞክራሲ መኖሩን አያመለክትም:: ተጨባጩ የዓለም ሁኔታ በአሁኑ ጊዜ የምርጫዎች መካሄድን ግድ እያለ በመምጣቱ ብዙ አምባገነኖች ምርጫ አካሄድን ብለው እየቀለዱ ያው 99 በመቶ ሕዝብ መሩን ብለው በማላገጥ አሸናፊ ነን ይላሉ:: ምዕራባውያን ደግሞ አጭበርባሪው አገዛዝ ወዳጃቸው ከሆነ ግድ የላቸውም-- ወንጀሉን ይቀበሉታል:: የወያኔን የ 1997ኡን እንደተቀበሉትና በቅርቡ የአሜሪካዋ የውጭ ጉዳይ ም/ ሃላፊ እንዳስ ደመጥችን ማለት ነው::

የወያኔ አገዛዝ የባዕዳን ሎሌ ነው:: ሀገርን ክብርን ሸጧል:: አሜሪካን ሊያስደስት ሶማሌን ወሮ ብዙ ሕዝብ አስጨርሷል--ጫኑኝ ልሸከም ባይ መጋዣቸው ነው:: ስለዚህም በመጪው ምርጫ ያው ማጭበርበሩን የሚቀበሉለት ናቸው:: በ1997 ኡ ምርጫ ተቃዋሚ ድርጀቶችን መራን ያሉ ግን የባዕዳን ሎሌ የነበሩ ግለሰቦች የሕዝብን ትግልና የሙት ከተማ አድማ እንዴት እንዳከሸፉተና

ከዚያም የወያኔ ተለጣፊ እንደሆኑ ታዝበናል። በአሁኑ ጊዜም በባዕዳን እየተሸረበ ያለው ሴራ ምስ ጢር አይደለም። ተቃዋሚ ነን የሚሉት ሁሉ ለወያኔ ተንበርክከው በምርጫው አጃቢ እንዲሆኑ ግፊት እየተደረገ ነው። ተቃዋሚዎች መሰረታዊ ቅድመ ሁኔታዎችን በማቅረብ ( ሁሉም የፖለ ቲካ እስረኞች ይፈቱ፤ የምርጫው ህግ ይቀየር፤ ነፃ የምርጫ ቦርድ ይቋቋም፤ ለነፃና ፍትሀዊ ምር ጫ የሚያስፈልጉት ሁኔታዎች ይሟሉ ወዘተ… የሚሉትን በማንሳት ትግል ማካሄድ አለባቸው።

በሌላ በኩል ደግሞ ሀቀኛ ሀገር ወዳድ ድርጅቶች በቅደሚያ ተጠናክረው ቀሰ በቀስ እያበሩ የጋራ ጥንካሬ ማግኘት ሲገባቸው አሁንም ተበታትነው ይገኛሉ። በየአቅጣጫው የተደረገውም ትብብር የትም አልደረሰም። እንዳንዶቹንም ወያኔ ሰርጎ በመግባቱ ጡንቻ አልባ አድርጓቸዋል።
በርካት ያሉትም አስመሳዮች ናቸው። በወያኔ የሚደጎሙ የሚሾፈሩ። ሊታገል የተነሳ ሕዝብም ትግሉ በአምልኩኝ ባዮች አስመሳዮች እንዳይደናቀፍ ጠንቅቆ መጠበቅ አለበት። የተመረቀ መስለ ው ት ከተረገመ ጋር ለሚውል ወዮለት ነው ነገሩ። ብልጭ ያለ ሁሉ ወርቅ እንዳይመስለን መጠንቀ ቅ ይገባል። መሪ የምንላቸውም የተፈተኑና ለመስዋዕትነት ዝግጁ የሆኑ የጀግነንት አርአያ መሆን አለባቸው። ባሳለፍናቸው የመከራና የትግል ዓመታት ብዙ አይተናል ተምረናልና ዳግም ልንሞ ኝ አይባንም። የወያኔን መሰሪነት አውቀናል። ትግሉ መራራ መሆኑን አውቀናል። የሕዝብ ነን ብ ለው፤ ከጎነንህ ነን ብለው ሕዝብን የካዱትንም አፈ ጮሌ ባንዳዎችንም ታዝበናል። በደም የገበየነ ውን ተመክሮ ሚዛን እንስጥ።

የወያኔን አገዛዝ በትግል አንኮታኩቶ ከመጣል ሌላ ምንም አማራጭ የለንም!
በቆራጥ ትግል ሀገራችንን እንታደግ፤ በወያኔ ላይም ድልን እንቀዳጅ!!